መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች

# ኢየሱስ 5000 ሰዎችን መገበ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Henok Estifanos

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

በርካታ የሐይማኖት መሪዎች (ፈሪሳውያን ተብለው የሚጠሩ) ስለ ኢየሱስ ውሸት ተናገሩ። አንዳንዶቹ ሊገድሉት እንኳን ይፈልጉ ነበር።



እርሱ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ
እንደሆነ አላመኑም ነበር፡፡
የእግዚአብሔር
ልጅ



እንደሆነ የሚያረጋግጡ
ታዕምራትን ቢሰራ
እንኳን አልተቀበሉትም፡፡

አንድ ቀን፤ኢየሱስ የገሊላን ባህር እየተሸገረ ነበር፡፡
ምናልባት ሁልጊዜ ከሚከቡት በርካታ ህዝብ ትንሽ
እረፍት ፈልጎ ይሆናል፡፡ ነገር
ግን ወዲያው ህዝቡ አገኙት፡፡
ኢየሱስ ታላላቅ ታዕምራትን
እንደሰራ አወቁ፡፡ ከኢየሱስ
ጋር መሆን ፈልገው
ነበር፡፡





ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እርሱ ተቀምጦ
ወደሚያስተምርበት ምንም ወደ ሌለው ተራራ
እየመራ ወሰዳቸው፡፡እጅግ በርካታ የሆነ
ህዝብ መምጣት ጀመረ፡፡
ወዲያው የአራት ሰዓት
ደረሰ፡፡ሁሉም ሰው
ተርቦ ነበር፡፡

ኢየሱስ ወደ ህዝቡ ተመለከተ "ይህ ህዝብ የሚመገበውን እንጀራ ከየት ነው የምንገዛው?" ብሎ ፊሊጶስን ጠየቀው፡፡ በዚህ ምንም የምግብ መሸጫ የለም፡፡ ኢየሱስ ያቀደው ምን ነበር?





"ይህን ሁሉ ህዝብ ለመመገብ በጣም ወጪ ያስወጣል" ብሎ ፊሊጶስ ለኢየሱስ መለሰት፡፡ ኢየሱስ እና ደቀመዛሙርቱ ብዙ የሆነ ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡"





እንድሪያስ የተባለው
ሌላኛው ደቀመዝሙር
(የስምዖን ጴጥሮስ
ወንድም ነው)
ለኢየሱስ እንዲህ
አለው፡"ህዚህ አምስት
ዳቦ እና ሁለት
እንጀራ ያለው አንድ
ልጅ አለ ..."

"... ነገር ግን ለዚህ ሁሉ ምን ያህል ይበቃሉ?" ምንም እንኳን ትንሹ ልጅ ምሳውን ለኢየሱስ ሊሰጥ ፈቃደኛ ቢሆንም- እንድሪያስ የትንሹ ልጅ ምሳ በርካታ ህዝብ ሊመግብ እንደሚችል
አላየም::



ኢየሱስም፤" ህዝቡ እንዲቀመጥ አድርጉ"፤ አለ፡፡ስለዚህ ሰዎቹ ተቀመጡ፤በቁጥር አምት ሺ ይሆናሉ፡፡ አስደናቂ ነው! አምስት ሺ! ያ በዚያ የነበሩትን ህጻናትን እና ሴቶችን እንኳን አያካትትም፡፡



በቀጣይ፤ደቦውን እና አሳውን ወሰደ፡፡ትንሹ ልጅ ኢየሱስን ታምኗል፡፡ እርሱ ምሳውን ለምን እንደፈለገ ወይም በምሳው ምን ሊያደርግ እንደፈለገ አላወቀም፡፡"ምሳዬን ብሰጥ፤ምሳ ሳልበላ እችላለሁ" ብሎ አስቦም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለኢየሱስ ሰጠው፡፡



ከዚያም፤ኢየሱስ ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ ለአምስት ዳቦ እና ለሁለት አሳ ነውን? አዎ!
ኢየሱስ እግዚአብሔርን
"አመሰግንሃለሁ"
አለ፤እና
ምግቡን
እንዲባርክ
ጸለየ፡፡



ከጸለየ በኋላ፤ኢየሱስ ዳቦውን
እና አሳውን ቆርሶ ለህዝቡ
ያድሉ ዘንድ ለደቀመዛሙርቱ
ሰጣቸው። በዚያን ጊዜ ህዝቡ
የኢየሱስ የሰራውን ታዕምር
ተመለከተ። እያንዳንዱ ሰው
የሚበቃውን ያህል ተመገበ።
ነገር ግን ደቦውና አሳው
አላለቀም ነበር።



ሁሉም ከተመገቡ በኋላ፤አሁንም በርካታ ዳቦ እና አሳዎች ተትረፍርፈው ነበር፡፡"ምንም እንዳይባክን የተራረፈውን ሰብስቡ ብሎ" ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው፡፡ ከአምስት ዳቦ ህዝቡ ሳይበላው የተራረፈው አስራ ሁለት ቅርጫቶችን ሞሉ፡፡



በዚያን ቀን፤ኢየሱስ በዚያ ትንሽ ልጅ ምሳ
5000 ሰዎችን መገበ፡፡ በሌላ ጊዜ፤በሰባት
ዳቦ እና ጥቂት አሳ 4000 ሰዎችን መገበ፡፡
ተራ ሰዎች ይህንን ምልክቶች በሚያዩ
ጊዜ፤እንደ ፈሪሳውያን
አልተናደዱም
ነበር፡፡



ነገር ግን "ይህ በእውነት ወደ ዓለም የመጣ ነብይ ነው" አሉ፡፡ እነርሱ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ተስፋ ተሰጥቶ የመጣ አዳኝ እንደሆነ አወቁ፡፡



ኢየሱስ 5000 ሰዎችን መገበ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዮሐንስ 6

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16